| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ድርሰት ፤ ጥርዮታዊ ፡ ትንታኔ ። |
| ርእስ ፤ | "የውሸት ፡ አኃዝ ፥ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ቋሚ ፡ ስልቱ ፡ ነው ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2013.001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | ተከታታይ ፡ ዐምድ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ጥርዮታዊ ፡ ትንታኔ ።

Economic Analysis | Analyse économique

## የውሸት ፡ አኃዝ ፥ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ቋሚ ፡ ስልቱ ፡ ነው ።

---

ያገራችን ፡ ሰው ፡ ወሬኛን ፡ "አባ ፡ ንፋው" ፡ ይለዋል ፤ ጕዳዩን ፡ እንደ ፡ ኳስ ፡ ስለሚነፋው ፡ ይመስላል ። ማስተንፈሻውም ፡ የዚያኑ ፡ ያኽል ፡ ቀላል ፡ ነው ፦ እውነቱን ፡ መንገር ።

*«ጠፍር ፡ በሊታ ፡ ብትኼድ ፥ ልጓም ፡ በሊታ ፡ መጣች»* ፡ እንዳለው ፥ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፡ የ 27 ፡ ዓመት ፡ "ፕሮፐጋንዳ" ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፥ ዛሬ ፡ ደግሞ ፥ የኢ.ሕ.ዴ.ግ.–ብልጽግና ፡ ፓርቲ ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፡ ለከት ፡ የለሽ ፡ ነጭ ፡ ውሸትን ፡ በእየምክንያቱ ፡ ሲነዛ ፡ ይውላል ። "የኹለት ፡ አኃዝ" ፡ እድገት ፡ የለመድነው ፡ ውሸት ፡ ነበር ፤ ዛሬ ፡ ደግሞ ፥ *«ዐምስት ፡ ቢልዮን ፡ ዛፎችን ፡ ባንድ ፡ ክረምት ፡ ተከልን»* ፡ የሚል ፡ ያበጠ ፡ ውሸት ፡ ተሰምቷል ። መቼም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ማወራኛዎች ፡ (የመንግሥትም ፡ ኾኑ ፡ የግል) ፡ አኃዛዊ ፡ መረጃን ፡ ለማጣራት ፡ አይደፍሩም ፥ ባር ፡ ባር ፡ ይላቸዋል ፤ ምክንያቱ ፡ አይታወቅም ። የዓለም ፡ ማወራኛዎችም ፡ ስለ ፡ ኢ.ሕ.ዴ.ግ.–ብልጽግና ፡ ፓርቲ ፡ ሲኾን ፥ የተለመደውን ፡ ጸጕር ፡ መሠንጠቃቸውን ፡ ትተው ፥ ወሬውን ፡ እንዳለ ፡ ሳያበጥሩት ፡ ከእነዐሠሩና ፡ ከእነጕድፉ ፡ ለዓለሙ ፡ ኹሉ ፡ ይነዙታል ። ምንም ፡ ጕዳዩ ፡ ተፈጥሮን ፡ የመከባከብ ፡ ደግኛ ፡ ሥራን ፡ ቢገልጽ ፥ ማጋነኑ ፥ የሚሸፍነው ፡ ሌላ ፡ ዐላማ ፡ መኖሩን ፡ ይጠቍማል ። ድብቁን ፡ ዐላማ ፡ ዐላሚዎቹ ፡ ያውቁታል ፤ እዚህ ፡ ላይ ፡ አንመራመርበትም ። ይልቁን ፥ ሕዝብ ፡ እንዳይሳሳት ፡ ያበጠውን ፡ ውሸት ፡ ኹሉ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ልናስተነፍሰው ፡ ይገባል ። ከድፍረት ፡ አይቈጠርብንና ፥ የኢትዮጵያ ፡ መዜንዎችንም ፡ አኃዛዊ ፡ መረጃን ፡ የመመርመር ፡ ባህልን ፡ እንዲያዳብሩ ፡ በዚህ ፡ አጋጣሚ ፡ ልናበራታቸው ፡ ይዳዳናል ።

በቀድሞ ፡ ዘመን ፥ አንድ ፡ ተማሪ ፡ መምህሩን ፦ ከመቶ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ አኃዝ ፡ ስንት ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፥ መምህሩ ፦ ሺሕ ፡ ነው ፡ አሉት ። ተማሪም ፦ ከሺሕ ፡ ቀጥሎስ ፧ ቢል ፥ መምህሩ ፦ ሚልዮን ፡ ነው ፡ አሉት ። ተማሪ ፡ አኹንም ፦ ከሚልዮን ፡ ቀጥሎስ ፧ ቢል ፥ መምህሩ ፡ መደምደሚያቸውን ፦ ከሚልዮን ፡ ወዲያማ ፡ ዝም ፡ ነው! አሉት ። የእኛም ፡ መዜንዎች ፡ አኹን ፡ ላይ ፡ ዝምን ፡ መርጠዋል ፤ የውሸት ፡ ቅዱስ ፡ ያለው ፡ ይመስል ፥ አርምሞን ፡ መምረጣቸው ፡ ይኾናል ።

ከቶ ፥ 5 ፡ ቢልዮን ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ፧ ስንት ፡ ነው ፧ ባለ 9 ፡ ዜሮ ፥ 5 ፡ ሺሕ ፡ ሚልዮን ፡ ነው ፡ ብንል ፥ ምናልባት ፡ አኃዙ ፡ ባእምሮ ፡ አይዘገንልን ፡ ይኾናል ። ዶክተር ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳያፍሩ ፦ ባለፈው ፡ ክረምት ፡ 5 ፡ ቢልዮን ፡ ዛፎችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አስተክያለኹ ፡ ብለዋል ። እነዚህን ፡ 5 ፡ ቢልዮን ፡ ዛፎች ፡ እስቲ ፡ ከሐሳብ ፡ ዓለም ፡ ወርደው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ቢተከሉ ፥ የሚያለብሱትን ፡ ብሔር ፡ (ምድር) ፡ እንከንዳላቸው ። [በነገራችን ፡ ላይ ፥ ከ 5 ፡ ቢልዮኑ ፡ ዛፎች ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ 50 ፡ ዛፎች ፡ ይደርሱታል ፡ ማለት ፡ ነው ። ባለፈው ፡ ክረምት ፡ ስንት ፡ ሰው ፡ ይኾን ፡ 50 ፡ ዛፎችን ፡ ይቅርና ፡ 5 ፡ ዛፎችን ፡ የተከለ ፧ ]


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።

እያንዳንዱን ፡ ዛፍ ፡ አንዱን ፡ ከሌላው ፡ በኹለት ፡ ሜትር ፡ ርቀት ፡ እንትከለው ፡ እንበልና ፥ ባንድ ፡ ኪሎሜትር ፡ ርዝመት ፡ 500 ፡ ዛፎችን ፡ እንተክላለን ። ወርዱን ፡ አንድ ፡ ኪሎሜትር ፡ ብናደርገው ፡ ደግሞ ፥ ባንድ ፡ ኪሎሜትር ፡ ማእዘን ፡–

500 * 500 =250'000

ዛፎችን ፡ ተከልን ፡ ማለት ፡ ይኾናል ።

በዚያው ፡ ባንድ ፡ ኪሎሜትር ፡ ወርድ ፡ ለ 1'240 ፡ ኪሎሜትር ፡ ዛፍ ፡ መትከሉን ፡ ብንቀጥል ፡ ደግሞ ፥ (በወፍ ፡ በረር ፡ ከደቡባዊቷ ፡ የድንበር ፡ ከተማ ፡ ከሞያሌ ፡ ተነሥተን ፡ እስከ ፡ ሰሜናዊቷ ፡ የቀይ ፡ ባሕር ፡ የድንበር ፡ ዳርቻ ፡ ራስ ፡ ካሰር ፡ ድረስ ፡ ማለት ፡ ነው) ፡–

250'000 * 1'240 = 310'000'000

ወይም ፡ 310 ፡ ሚልዮን ፡ ዛፎች ፡ ይተከላሉ ፡ ማለት ፡ ይኾናል ። በሌላ ፡ አነጋገር ፥ ባ 1 ፡ ኪሎሜትር ፡ ግንባር ፣ ከሞያሌ ፡ ተነሥተን ፥ ሀዋሳን ፣ ዐዲስ ፡ አበባን ፣ ላሊበላን ፣ አኵስምን ፣ አስመራንም ፡ እያለበስን ፡ ዐልፈን ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ካሰር ፡ የቀይ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻችን ፡ ድረስ ፡ 310 ፡ ሚልዮን ፡ ዛፎች ፡ ይተከላሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። ኾኖም ፥ 4 ፡ ቢልዮን ፡ 690 ፡ ሚልዮን ፡ ገና ፡ የሚተከሉ ፡ ዛፎች ፡ ይቀሩናል ። እነዚህንም ፡ ለመትከል ፥ ወርዱን ፡ ካ 1 ፡ ኪሎሜትር ፡ ግንባር ፡ ወደ ፡ 16 ፡ ኪሎሜትር ፡ ግንባር ፡ ማስፋት ፡ ይኖርብናል ። እነዚህ ፡ ባ 16 ፡ ኪሎሜትር ፡ ግንባር ፡ በ 1'240 ፡ ኪሎሜትር ፡ ርዝመት ፡ የሚተከሉ ፡ ዛፎችም ፡ 19'840 ፡ ኪሎሜትር ፡ ማእዘን ፡ የሚያኽል ፡ አገርን ፡ በጥቅጥቅ ፡ ደን ፡ ሸፈኑት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ይኾናል ፤ ይህም ፡ እስራኤልን ፡ የሚያኽል ፡ ሀገር ፡ ያለብሳል ።

ከብዙ ፡ ሐተታ ፡ ይልቅ ፡ የሚከተለው ፡ ቢጋር ፡ ኹኔታውን ፡ አጠቃሎ ፡ ይከሥትልናል ።




*ቢጋር 1: ዐምስት ፡ ቢልዮን ፡ ዛፎች ፡ ተተክለውበታል ፡ ስለተባለው ፡ ምድር ፡ መጠን ፡ ሥዕላዊ ፡ መግለጫ ።*

*ዐምስት ፡ ቢልዮን ፡ ዛፎች ፡ ተተከሉ ፡ ማለት ፥ ለ 1'240 ፡ ኪሎሜትር ፡ ርዝመት ፥ ባ 16 ፡ ኪሎሜትር ፡ ግንባር ፡ 8'000 ፡ ዛፎች ፡ በእየኹለት ፡ ሜትሩ ፡ እየተተከሉ ፥ ከደቡባዊቷ ፡ ድንበር ፡ ከተማ ፡ ከሞያሌ ፡ ተነሥተን ፡ እስሜናዊቷ ፡ የቀይ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ካሰር ፡ እንደርሳለን ። በደን ፡ የተሸፈነው ፡ ወለልም ፡ 19'840 ፡ ኪሎሜትር ፡ ማእዘንን ፡ ያክላል ፥ ይህም ፡ የኢትዮጵያን ፡ የደን ፡ ሽፋን ፡ ባ 50% ፡ ያሳድጋል ፥ ወይም ፡ እስራኤልን ፡ የሚያኽል ፡ ሀገር ፡ ይሸፍናል ። እያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፥ ሕፃን ፣ ሽማግሌ ፥ ወንድ ፣ ሴት ፥ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ 50 ፡ ዛፎችን ፡ ተክሏል ፡ ማለት ፡ ይኾናል ። በእውን ፡ ግን ፥ የዚህ ፡ አንድ ፡ ዐሥረኛ ፡ (500 ፡ ሚልዮን ፡ ዛፎች) ፡ መተከላቸው ፡ ያጠራጥራል ።*

ችግኙስ ፡ ከየት ፡ መጣ ፨ ብሎ ፡ ለሚጠይቅም ፥ ከ 3'000 ፡ በላይ ፡ የችግኝ ፡ ማፍሊያ ፡ ጣቢያዎች ፡ በመላ ፡ ሀገሪቱ ፡ መቋቋማቸው ፡ ተነግሯል ። መልካም ! እያንዳንዱ ፡ የችግኝ ፡ ማፍሊያ ፡ ጣቢያ ፡ ባማካይ ፡ 1 ፡ ሚልዮን ፡ 667 ፡ ሺሕ ፡ ችግኞችን ፡ አፍልቷል ፡ ማለት ፡ ነው ።

የዕቅዱ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ባጀትስ ፡ ስንት ፡ ነበር ፨ ገንዘቡስ ፡ ከየት ፡ መጣ ፨ ርግጥ ፡ ነው ፥ ዶክተሩ ፡ ዕቅዳቸውን ፡ ለይፋው ፡ ሲያሳውቁ ፥ አንድ ፡ አድናቂ ፡ የምዕራብ ፡ ዓለም ፡ መሪ ፡ (ያውም ፡ በ"ኮሮና" ፡ ዘመን) ፡ *«150 ፡ ሚልዮን ፡ € ፡ ወይም ፡ 6 ፡ ቢልዮን ፡ ብር ፡ ቃል ፡ ገብቶልኛል»* ፡ ማለታቸው ፡ ይታወሳል ። ኾኖም ፥ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ገንዘቡ ፡ መግባቱንና ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ መዋሉን ፡ ተከታትሎ ፡ ያረጋገጠ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።

መዜንው ፡ የለም ።

አንድ ፡ ዛፍ ፡ ለመትከል ፥ ከችግኝ ፡ ማፍላቱ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ማጓጓዣውና ፡ እስከ ፡ ተከላው ፡ ድረስ ፥ ወጪ ፡ አለው ፤ ጠቅላላ ፡ ወጪው ፡ ከቶ ፡ ስንት ፡ ይደርሳል ፧ መቼም ፡ ሲያንስ ፡ ቢውል ፥ በችግኝ ፡ ካ 5 ፡ ብር ፡ አያንስም ፤ በድምር ፡ 25 ፡ ቢልዮን ፡ ብር ፡ ማለት ፡ ነው ። እውነተኛው ፡ ወጪ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በብዙ ፡ ዕጥፍ ፡ እንደሚበልጥ ፡ ዝርዝር ፡ ስሌቱን ፡ ያሰሉ ፡ አጥኒዎች ፡ አረጋግጠውልናል ። ከመዋቅራዊ ፡ እና ፡ ከሰው ፡ ኀይል ፡ ወጪ ፡ ሌላ ፥ ዋናው ፡ የወጪ ፡ አርእስት ፡ ማጓጓዣው ፡ ነው ። እንደሚገመተው ፥ አብዛኛው ፡ የተከላ ፡ ቦታ ፡ በችግኝ ፡ ማፍሊያ ፡ ጣቢያ ፡ አካባቢ ፡ አይደለም ፤ ዐሥር ፡ ዐሥራምስት ፡ ኪሎሜትር ፥ ከዚያም ፡ በላይ ፡ በሚያስኬድ ፡ ገደላማ ፡ እና ፡ የተራቈተ ፡ አካባቢ ፡ ተመርጦ ፡ እንደተተከለበት ፡ ተነግሮናል ። ዐምስት ፡ ቢልዮን ፡ ችግኞችን ፡ ለማጓጓዝ ፡ ከ 1 ፡ ሚልዮን ፡ እስከ ፡ 1.5 ፡ ሚልዮን ፡ የጭነት ፡ መኪና ፡ መመላለሶች ፡ ተደርገዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ለነዳጅ ፡ ወጪና ፡ ለነጂ ፡ ኪራይ ፡ ባማካይ ፡ 1'000 ፡ ብር ፡ ቢታሰብ ፥ በድምሩ ፡ ለማጓጓዣ ፡ ብቻ ፡ እስከ ፡ 1.5 ፡ ቢልዮን ፡ ብር ፡ ወጥቷል ። ሌሎች ፡ ተያያዥ ፡ ወጪዎች ፡ ተደምረው ፥ ለእንያንዱ ፡ ችግኝ ፡ ተከላ ፡ ቢያንስ ፡ ከ 50 ፡ ብር ፡ እስከ ፡ 150 ፡ ብር ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ይገመታል ፤ ይህም ፡ ከ 250 ፡ ቢልዮን ፡ ብር ፡ እስከ ፡ 750 ፡ ቢልዮን ፡ ብር ፡ ማለት ፡ ይኾናል ፥ ወይም ፡ የመንግሥትን ፡ ዓመታዊ ፡ ባጀት ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ማለት ፡ ይኾናል ።

አገሪቱ ፥ ሳትወድ ፡ በ"ክልል" ፡ ተከልላለችና ፥ እኛም ፡ ሳንወድ ፡ "ክልል" ፡ ብለን ፡ እንጥራቸውና ፥ ካ 5 ፡ ቢልዮኑ ፡ ችግኝ ፥ ለመኾኑ ፡ የእያንዳንዱ ፡ "ክልል" ፡ ድርሻ ፡ ስንት ፡ ነበር ፧ የ"ሶማሌ ፡ ክልል" ፡ አመራር ፡ 2 ፡ ሚልዮን ፡ ችግኞችን ፡ (0.04%) ፡ ሊተክል ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ ነበር ፤ ... ፡ የ"ገምቤላ ፡ ክልል" ፡ አመራርም ፡ እንደዚሁ ፡ 1 ፡ ሚልዮን ፡ (0.02%) ፡ ሊተክል ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ ነበር ፤ ... ፡ የ"በኒ ፡ ሻንጉል ፡ ጉምዝ ፡ ክልል" ፡ አመራር ፡ በፀረ ፡ ሀገራዊ ፡ ዘመቻና ፡ በሽፍትና ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ተበጥብጧል ፥ 1 ፡ ሺሕ ፡ ዛፍ ፡ መትከሉ ፡ ያጠራጥራል ፤ እንደዚሁ ፡ የ"ኦሮሞ ፡ ክልል" ፡ አመራር ፡ በፀረ ፡ ሀገራዊ ፡ ዘመቻ ፣ በሽፍትና ፡ በሙስና ፡ ተሰሚነቱን ፡ ዐጥቷል ፥ ከማንፏሸር ፡ በቀር ፡ የሚፈይደው ፡ ነገር ፡ አልነበረም ፡ ... ።

የተዋሹልን ፡ 5 ፡ ቢልዮን ፡ ዛፎች ፡ እውን ፡ ባለፈው ፡ ክረምት ፡ ተተክለውልን ፡ ቢኾን ፡ ምንኛ ፡ በተደሰትን ፡ ነበር ፤ ለክርሞም ፡ በገንዘብም ፡ በጕልበትም ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ በደገፍን ፡ ነበር ።

... ፡ "ላለፈው ፡ ክረምት ፡ ቤት ፡ አይሠራምና" ፥ እስቲ ፡ ለወደፊቱ ፦ አንድም ፥ የማይመስል ፡ ነገርን ፡ ቃል ፡ አንግባ ፤ አንድም ፥ የሚነገሩንን ፡ አኀዞች ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ብሎ ፡ ከመቀበል ፡ ይልቅ ፥ ሒሳብ ፡ ማሰቢያችንን ፡ ታጥቀን ፡ በእየቦታው ፡ ተዘዋውረን ፡ የነገሩን ፡ እውንነት ፡ እናረጋግጥ ።

ነገሩን ፡ እንደተነገረው ፡ እውነት ፡ ኾኖ ፡ ብናገኘው ፥ ይህኑ ፡ ለሕዝብ ፡ የማረጋገጥ ፤ እውነት ፡ ኾኖ ፡ ባናገኘው ፡ ደግሞ ፥ ሐሰትነቱን ፡ ለሕዝብ ፡ ስሜት ፡ የማስታወቅ ፡ ሞያዊም ፡ ኅሊናዊም ፡ ሀገራዊም ፡ ግዴታ ፡ አለብን ፤ ሕዝብ ፡ የሚያደርገውን ፡ በተረዳ ፡ ያደርጋል ።

*«የሌባ ፡ ዐይኑ ፡ ደረቅ ፥ መልሶ ፡ ልብ ፡ ያደርቅ»* ፥ ዐምስት ፡ ቢልዮኑን ፡ በይሉኝታ ፡ ዐለፍነው ፡ ስንል ፥ *«ደግሞ ፡ ለክርሞ ፡ 20 ፡ ቢልዮን ፡ አስተክላለኹ!»* ፡ ብለውን ፡ ቁጭ ! የከርሞ ፡ ነገር ፡ መች ፡ ተያዘና ፧ ለዓመት ፡ ቀርቶ ፡ ለዐዳርም ፡ መተንበዩ ፡ አላስተማምን ፡ ብሏል ።

የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ይኸው ፡ ነው ፤ ከጭቈናና ፡ ከ"ከፋፍለኽ ፡ ግዛ" ፡ ሌላ ፥ ስልቱ ፦ አንድም ፥ የተስፋ ፡ ጕምን ፡ ማስጨበጥ ፡ ነው ፤ አንድም ፥ ዐይን ፡ ያወጣ ፡ ውሸትን ፡ መደጋገም ። እኛስ ፡ አይበቃንም ፡ ወይ ፧ እስከ ፡ መቼ ፡ የዓለም ፡ መሣለቂያ ፡ እንኾናለን ፧ ውንብድናን ፡ የመሸከም ፡ ባህልም ፡ ዕዳም ፡ የለብን ። እትከሻችን ፡ ላይ ፡ በልመና ፡ አልወጣም ፥ በልመናም ፡ አይወርድ ፤ በውድ ፥ አለዚያ ፡ በግድ ፡ እኛው ፡ ከትከሻችን ፡ ማውረድ ፡ አለብን ። ለሥልጡንሕዝብ ፥ በወደደው ፡ ዐዳር ፡ ከማደር ፡ በቀር ፥ በውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ "በጎ ፡ ፈቃድ" ፡ ማደር ፡ መቼም ፡ ቢኾን ፡ አይገባው ※


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።